# በኢትዮጵያ ስለሀገር መጸለይም ያስወነጅላል!

ይሄይስ አእምሮ

የትራንስፎርሜሽኑ መዘዝ በሚል ርዕስ ያወጡትን ጽሑፍ አይቼዋለሁ:: ያሉት ሁሉ ትክክል ነው:: ነገር ግን የእኛ ፖለቲከኞች ላለመተባበር መተባበርን የመረጡ ይመስላል:: ስለዚህ ወያኔ ባሻው መንገድ ኢትዮጵያን ይገዛል:: ከእንግዲህ ሕዝባችን የቀረው የአምላክን ተአምር መጠበቅ ይመስለኛል:: <u>የሲቭክ ማህበራት ወይም ሌሎች ተመሳሳይ ድርጅቶች አጠቃላይ የጸሎት ጥሪ ቢያደርጉ</u> የተሳካ ውጤት አይገኝም ብለው ያምናሉ? ይህ ደግሞ በሀገር ቤትም በውጭም በቀላሉ ሊከናወን ይችላል የሚል ግምት አለኝ:: በጸሎቱ ላይ በመገኘት ኢትዮጵያውያን ሀገራቸው በችግር ውስጥ እንዳለች እንደሚያምኑ ለማንም ወገን ያረጋግጣሉ:: ዛሬ ወሬው ሁሉ በተደናበረበት ወቅት ጥርት ያለው የኢትዮጵያውያን ሀሳብ ተለይቶ መታወቅ አለበት::

እኔም እንደው የሀገሬ ነገር አንጀቴን ቢበላኝ እንጂ በውጭም በሀገርም ያሉ ኢትዮጵያውያን ለነጻነት የማይፈነቅሉት ነገር አይኖርም ብዬ አምናለሁ:: ለማንኛውም ሀሳቤን ለአንድ ሰው ማጋራቴ ትንሽ ተንፈስ ያደርገኛል:: በሌላ ጽሑፍ እንደማገኞት ተስፋ አለኝ:: (ሠረዝ የተጨመረ)

**በቅድሚያ ውድ ልጃችንና እህታችን ወ/ት ብርቱካን ሚዴቅሳ ከጠባቡ እሥር ቤት ወጥታ ወደ ሰፊው እሥር ቤት እኛው ዘንድ በመቀላቀልዋ የተሰማኝን ደስታ በዚች አጋጣሚ እንድገልጽ ይፈቀድልኝ፤ እንኳዋን ደስ ያለን:: መፈታትዋ ትልቅ ነገር መሆኑ እንዳለ ሆኖ ትግሉ ተጀመረ እንጂ ገና ዕልባት ስላላገኘ በመለስተኛ ደስታ ዋናውን ድል እንደማንዘነጋ ሁላችን የምንጋራው እምነት መሆኑን እረዳለሁ:: ምንም ነገር የሚሳነው ነገር የለምና አንድዬ በጀመረው ገፍቶበት አለፍርድ ለዕድሜ ይፍታህ ከተከረቸምንበት የወያኔ እሥር ቤት ነጻ ያውጣን:: በዓለሙ ዙሪያ እንደጨው ዘር የተበተንነውንም ዜጎችዋን በአዲስ መልክ በሚቀድሳት የኢትዮጵያ ምድር ያሰባስበን:: አሜን::**

- ❖ በሰማያዊ የተቀለሙ አንዳንድ ፊደላት ጠብቀው የሚነበቡ ናቸው::

በመግቢያነት የተጠቀምኩበት አስተያየት በበቀደም ለታው መጣጥፌ በሰጠሁት የኢሜል አድራሻ ከተላኩልኝ አስተያየቶች ከጂቡቲ አንዱዋ እህት የመየለችልኝ ነው - ምንም ነገር ሳልጨምር ወይም ሳልቀንስ ነው ያስቀመጥኩት:: በዚህ አጋጣሚ ውድ ጊዜያቸውን ሰውተው ከየድረ ገጾቻችን ያቺን ጽሑፍ ሳነበቡና ገምቢ አስተያየቶቻቸውን ለላኩልኝ (ለምሳሌ በበሳል ጽሑፎቹ የምናውቀው ሮቤል አባቢያ፣ ንጉሤ ጋማ እና ሌሎችም ስማችሁን ለመጥራት ከደኅንነት አንጻር ፈርቼ የተውኩት) ወገኖቼ የከበረ ምሥጋናየ በነዚሁ የወቅቱ ብቸኛ የትግል ወኔ መቀስቀሻና ሀገራዊ ብሶትን መጋሪያ አውታሮቻችን አማካይነት እንዲደርሳቸው በትህትና እጠይቃለሁ:: ከጊዜው የትግል ሥልቶች አንዱ የሀገራችን ቲቪና ሬዲዮ በኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪካዊ ጠላቶች እጅ ገብቶ ለውሸት ማራገቢያነት እዬዋለ በመሆኑ በነዚህ የቁርጥ ቀን ደራሽ የድረ ገጽ ባለሞያዎችና ጋዜጠኞች ስለሀገር ምንም ሳያውቁ ደንዝዞ ከመቀመጥ ወቅታዊ መረጃን ማግኘት ነው:: ከመረጃ የራቀ ሰው ከሀገር ቀርቶ ከራሱም የራቀ ለመሆኑ በድንገት የሚከሰትን አንዳች አደጋ ለማምለጥ የሚደረግን ጥረትና የጥረቱንም ስኬታማነት ዋቢ በማድረግ አስረግጦ መናገር ይቻላል:: ፈረንጆቹ፤ "Forewarned is forearmed"ይላሉ አስቀድሞ የመንቃትን ጠቀሜታ ለማጠየቅ:: እናም ሁላችንም በያለንበት ስለሀገራችን ወቅታዊ ትክክለኛ ገጽታ ለማወቅ ብንጥር መልካም ነው እላለሁ:: ይሄ ደግሞ ውዴታ ብቻ ሳይሆን ከግዴታዎቻችን ሁሉ ታላቁ ግዴታችን ነው:: «በማን ላይ ቆመሽ...» እንዲሉ ነውና ምንም እንኳዋን ለጊዜው ሥጋዊ ድሎት ቢኖረንም እንደ መጽሐፉ «ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም»ና ሀገራችንን ዘወትር ልናስባት ራሳችን ለራሳችን ቃል እንግባ - ይህን የምለው ለነአባ ግዴለሾችና ለነሆድ አምላኩ እንጂ የሀገራቸው አንገብጋቢ ጉዳይ እንደ'ግር እሳት ሌት ከቀን ለሚፈጃቸው ውድና ብርቅ ዜጎች እንዳልሆነ አንባቢ ይረዳልኛል ብዬ አምናለሁ:: ጊዜው የነጻነት ትግሉ ተፋፍሞ እንዲቀጥል በጉጉት የሚጠበቅበትና ጠቃሚው ፍሬ ከንፋሹ እንዲለይ የታሪክ ዐውድማ እየተለቀለቀና ለውቅያው እየደረሰ ያለበት - ከዚያም እንደስከዛሬው ሁሉ በጅምላ እየተግበሰበስንና ብዙዎች በጥቂት ኅሊናቢስ አማጊዶች እዬታመስን የምንጉዋዝብት አስቀያሚ ሁኔታ የሚቋጭበት - ፈጣሪም ምንዱባንና ግፉኣን ፍጡራኑን ሊጎበኝ የትንቢቱ ፍጻሜ ጭላንጭል የሚታይበት ጊዜ ነው:: በዚህም ምክንያት የመሞጋገሻውና የመመሰጋገኛው ወቅት ገና ስለሆነ እንጂ ስለእስስቶቹና ስለሆዳሞቹ ጅቦች ሳይሆን ስለልባሞቹ የኢትዮጵያ አለኝታ ልጆች አሁን ብዙ ማለት በተቻለ ነበር:: ወትሮም ቢሆን

የእናት ሆድ ዥንጉርጉር ነውና የአንድ ማኅበረሰብ ስብጥር አንዱ ገዳይ ሌላው ሟች፣ አንዱ አሳዳጅ ሌላው ተሳዳጅ፣ አንዱ አ*ዳ*ኝ ሌላው ታ*ዳ*ኝ፣ አንዱ አገር ሻጭ ሌላው የነጻነት ቤዛ ፣ አንዱ ለማኝ ሌላው መፅዋች፣ አንዱ ፈሪ ሌላው ዱለኛ . . . መሆኑ የታወቀ ነው:: ሆኖም የስብጥሩ አሉታዊ ሚዛን እኛ ሀገር ሲደርስ ክፉኛ አጋደለና ሀገራችን ልትጠፋ በጣት የሚቆጠሩ ሐሙሶች የቀሩ ይመስላል፤ ግን አይዞን - እንደወደቅን አንቀርም፤ ወላድ በድባብ ትሂድ እንነሳለን:: እርግጥ ነው - ጊዜ ያዋርዳል፤ ጊዜ ያከብራል:: ልብ ማለት ያለብን ትልቅ ቁም ነገር መከራም ሆነ ደስታ አያያዝን የሚጠይቁ መሆናቸውን ነው:: አገኘሁ ብሎ አላግባብ ጮቤ መርገጥ ወይም አጣሁ ብሎ አንገትን ደፍቶ መቆዘም ሁለቱም የጤነኝነት ምልክቶች አይደሉም:: እኛም «አጣን እንጂ አልደኸየንም» ብለን እንመን - እውነትም ነው:: ትልቁ ድህነት የአእምሮ ድህነት ነው - ከዚያ ዓይነቱ አስነዋሪና አዋራጅ ድህነት መጠንቀቅ በስህተት ገብተንበትም ከሆነ በአፋጣኝ ለመውጣት መሞከር ተገቢና ጊዜ የማይሰጠው ጉዳይ ነው:: ከሰው የሚያበሰና ጮማ ይልቅ የራስ ያሉት ጎመን ይበልጣል - ነባሩ ብሂልም «ጎመን በጤና» ሲል ይህን አመክንዮ እንደሚያጸድቀው::

በነገራችን ላይ እንኩዋን ለሰሞኑ የአቶ መለስ አሻንጉሊት ፓርላማ ሹም ሽር በሰላም አደረሳችሁ ብዬ መጀመር ሲኖርብኝ ያን ባለማድረጌ ይቅርታችሁን:: አሮጌው ወይን ባዲሱ አቅማዳ እየተጋባ እንደሆነ ሰዎች አወሩልኝ - እኔማ ከኢሕአዴግ ሚዲያ ምን የሚረባ ነገር አገኛለሁ ብዬ በተወደደ ጤንነት ዐይንና ጆሮየን ላባክን? የሌሎች ሰዎችም መከታተል ይደንቀኛል:: «እከሌ ወርዶ እከሌ ተተካ፤ፐ! እንዴት ዓይነቱ ‘ብሬናም’ መሰላችሁ!» እያሉ ሲያወሩ ስሰማ ልቤ ይደማል፤ ከመለስ ይልቅ ታዲያ ለነሱ አዝናለሁ - ስንትና ስንት የዋህ አለ መሰላችሁ በሁኔታዎች የፊት ለፊት ቅባዊ ገጽታ(face value) እየተታለለ እውነት እንደራቀችው የሚኖር:: መለስማ እየሠራ ያለውን የሚሠራው ለዘዴው ነው፤ሥዩም ተሸሮ ኃይለ ማርያም «ቢሾም» የገማው አናት እዚያው ተጎልቶ በቀጭንዋ የሥልክ ሽቦና በሞባይል ያፈተተውን ማድረግ እስከቀጠለ ድረስ የሎሌ መለዋወጥ ትርጉሙ ምንድነው? ጭንቅላት እንጂ ማሰቢያ አንጎል የሌላቸው ማይማን አድር ባዮችን ከወንበር ወንበር የሚያቀያይረው እንደጥንታውያኑ አጤዎች የዕድሜ ልክ ንጉሥ ሊኮን አይደል ጥረቱ? ኢትዮጵያም የሱና የመሰል ባንዳዎች የማትነጥፍ ጥገት እንደሆነች ስታነባ ልትዘልቅ አይደል በውጤቱ? እዚህ ላይ የሰውን የወያኔ ሚዲያ ክትትል ስታዘብ «የጉልቻ መለዋወጥ ወጥን አያጣፍጥም» እያለ የጨዋታን ለዛ በሚያደምቅ ኅብረተሰብ መሀል መፈጠሬን ወደመርሳት ደረጃ የምደርስበት ጊዜ መኖሩን ልሸሽጋችሁ አልፈልግም:: ባይገርማችሁ በሕዝብ ገንዘብ የተቋቋመ መገናኛ ብዙኃን በራሱ በሕዝቡ ላይ መቀለጃና ማሾፊያ ሆንዋል:: ቀልድ ስላችሁ የምሬን ነው - ደምበኛ የሕጻናት ‘ቃ ‘ቃ መጫወቻ:: ተቋሙም እኛም ስናሳዝን!

እዚች ቦታ ስደርስ አንድ ነገር ትዝ አለኝ - መቀለጃ የመሆናችንን ነገር በተመለከተ:: ወያኔ የኢትየጵያን ሕዝብ ያዋረደ እየመሰለው ራሱን የሚያቀሉትና ለዓለማቀፍ ትዝብት ሳይቀር የሚዳርጉት ብዙ አሳፋሪ ድርጊቶችን አከናውኖኣል፤ ይህን የጅላጅል ድርጊቱን አሁንም በባሰ ሁኔታ ቀጥሎበታል:: «የድንጋይ ማምረቻ» በመባል ከሚታወቀው የሲቭል ሰርቪስ ኮሌጅ በኮሌጁ ፕሬዝደንት ቀጭን ትዕዛዝ የነበሩዋት የ’F’ ውጤቶች ወደቆንጆ ውጤት ተለውጠውላት በግድፍድፍ/በድግፍግፍ/ የተመረቀች የበረሃ ዓይጥ፣ የቀዳሚ እመቤትነት ማዕረጉ ሳያንሳት በሀገሪቱ የጨረባ ተዝካር መሰል ወያኔያዊ የሥልጣን ክፍፍል የሚኒስትር ማዕረግ ማግኘቷ «በሀገሪቱ ከእርስዋ የበለጠ የተማረ ሰው ጠፍቶ ነውን?» ያሰኛል:: የባልዮውን ይሉኝታ ማጣትናሀፍረተቢስነት ለሚልዮንኛ ጊዜ በጉልህ ያሳያል:: ጓደኞቹስ ምን ይሉት ይሆን ጃል? ለነገሩ አእምሮ ያለው የረባ ጓደኛ ሲኖረው አይደል? ሌላው ማፈሪያ ነገር ከ80 ሚሊዮኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ መሃል ከእርሳቸው የተሻለ ሰው ተፈልጎ ታጥቶ (ዋና ሥራቸው እንግዳ መቀበልና መሸኘትም ቢሆን) በአካልም በአዕምሮም በመንፈስም የሞቱ ኢትዮጵያዊ ኤርየል ሻሮል በፕሬዝደንትነት ሲሾሙልን ክፉኛ መ<u>ና</u>ቃችንን ያወቅነው ያኔ ነው:: ሻሮል ሰመመናቸው ውስጥ ገብተው ይሙቱ ይዳኑ ሳይታወቅ በዚያው ደብዛቸው ጠፍቷል:: አንድ እግራቸው መቃብር ውስጥ የሚገኘው «ልጣቸው የተራሡ ጉድጓዳቸው የተማሰ» የኛው «መሲሕ» ግን እንዲያነ<u>ቡ</u> የሚሰጣቸውን ወረቀት በቅጡ ለመያዝ እንኩዋን አቅም እያጡ ሲንቀጠቀጡና አንደበታቸውም እየከዳቸው ማንበብ ሲያቅታቸው ወያኔ ሊያዝንላቸውና ሊያሰናብታቸው አልፈቀደም:: እሳቸውም አያፍሩም ከፈጣሪያቸው ጋር ታርቀው በንስሃም ታጥበው ለነፍሳቸው ድኅነት መዘጋጀት ሲገባቸው በጅጅትና ዕድሜያቸው ሀገር «ይመራሉ»:: እሳቸውም እኛም የመለስ መጫወቻ መሆናችን አናሳዝንም?

ሌላ አንድ ነገር ደግሞ አሁን ትዝ አለኝ:: ትናንት ማታ የነዳጅ ዋጋ ጨመረ አሉ - ተራ ቤንዚን በሊትር ብር 13.88 ሆነ - ደርግ ሊወርድ አካባቢ ብር 1.50 ነበር መሰለኝ:: አንዱን « ሚስትህ ወንድ ወለደች?» ብሎ ይጠይቀዋል አሉ ጓደኛው፤ «ማንን ወንድ ብላ?» ይለዋል ሲመልስለት -

እንደማሽላዋ አንጀቱ አርሮ በጥርሱ እየሳቀ:: ወያኔ ማንን ወንድ ብሎ ግርፋቱን ያቁምልን? አሁንና ለጊዜው ማንንም!

የሆነ ሆኖ ኑሮ ተሰቀለ፤ ዱሮውንም እንደተሰቀለ ነበር:: ይህን መንግሥት ለመጣል አምስተኛ ረድፈኞች በንግዱ ዘርፍ ተሰማርተው ጦርነቱን እየተተጋተጉ መሰለኝ:: በጦርነቱ እየተጎዳ ያለው ግን ሕዝቡ ነው:: የሁሉም ሸቀጦች ዋጋ ሰማይ ደርሱዋል:: ከዘይትና ከቀይና ነጭ ሽንኩርት አቅም በአሁኑ ወቅት በቅደም ተከተላቸው በሊትር ወይም በኪሎ ብር 35፣ 12 እና 35 ሆነዋል፤ እንዲህ ያለ የኑሮ ውድነት ታይቶ ቀርቶ ተሰምቶም አይታወቅም:: አካሄዳችን ወደ ዚምባብዌና ወደ ቀድሞዋ የሁለተኛው ዓለም ጦርነት ጀርመን ወይም ወደ ዴ. ሪ. ኮንጎና ሶማሊያ መሰለኝ:: ዲያስፖራዎች ጉዳችሁ ፈላ:: የምትልኩት ገንዘብ የረባ ነገር ሳይሠራ ወደ ነጋዴው ኪስ ሰተት ብሎ እየገባ ነው:: መቶ ብር ዘርዝረሽ ትርጉም ያለው ነገር ሳትሠሪበት በቅጽበት ውስጥ ይጠፋል:: የት ጣልኩት ብለሽም ልትጨነቂ ትችያለሽ:: በሌላ ወገን ከሰዓት በኋላ ገና ባንዲራ ሳይወርድ - ባንዲራ አለን ብለን እናስብና - በየመጠጥና ሉካንዳ ቤቶቹ ተሰግስጎ ጮማ የሚቆርጠውንና ድራፍትና ቢራውን የሚኮመኩመውን፣ በአውራ ጎዳናዎች በሚርመሰመሱት ዕንቁላል የሚመሳሰሉ የቤትና የመስክ አውቶሞቢሎች የሚንፈላሰሰውን የሰው ብዛት ስናይ በርግጥ ኢትዮጵያ ውስጥ ነው ያለሁት? ያስብላል:: ሰው ተስፋ ቆርጦኣል መሰለኝ ባለችው አሥረሽ ምቺው ማለትን አጥብቆ ይዞ ከራሱ ጋር የጦፈ ጦርነት ገጥሞኣል:: መጠጥ በአሁኑ ወቅት የብዙዎች መደበቂያና ማኩረፊያ ምሽግ በመሆን ታሪካዊ የሕዝብ ተገንነቱን በማረጋገጥ ላይ ይገኛል:: የወያኔን ጊንጣዊ የጅራፍ ንድፊያ እየተጋፈጥን ያለነው አቅማችን የሚፈቅድልን በድሃዎች ሠፈር በመለኪያ አንድ ብር ከምትሸጠው ትንሹዋ ‘ካታማይሲን’(‘ሲስተር ጤናየ’ - ያበሻ ካቲካላ) ጀምሮ ከንፈር ለማያርስ አንድ መለኪያ 15 ብርና ከዚያ በላይ እስከሚከፈልበት ዊስኪ እየጠጣን በብርጭቆ ውስጥ መሸገን ነው:: ሞቅ ሲለንም የፍርሃት በርኖሳችንን ለጊዜው ወለቅ አድርገን ከሚመስለን አጠገባችን ያለ ሰው ጋር የወያኔን መንግሥት ጥምብ እርኩሱን እናወጣዋለን - በሞኝ አንግሥ ካባ ተጀቡነን ማንን ልንፈራ? ቢሆንም ግን በጣም ተጠንቅቀን ነው፤ «ብርቱካንን ያየ የወያኔን ሰላይ ሲያይ በረዬ» አይደል አዲሱ ተረት? የጆሮው ብዛት በሰው ልክ ስለሆነ ጥንቃቄ በጣም ወሳኝ ነው:: እንኩዋንስ በፖለተካ ምክንያት ታሥረህ ይቅርና በተራ ሁከት ሳቢያ ብትታሠር ዞሮ የሚያይህ የለም፤ ሕግም በፍጹም አይሠራም፤ እዚያው ዘብጥያህ ወርደህ ትበሰብሳታለህ:: አካሄዳችን እጅግ አደገኛ ነው:: «ጸጉራም ውሻ አለ ሲሉት ይሞታል» እንዲሉ ከአጠቃላዩ ሕዝብ በጣም ጥቂቱ ከዚህም ውስጥ ብዙው በተስፋ መቁረጥ የባዶነት ስሜት፣ አንዳንዱም በሙስና የሚዘርፈውና በንግድ ሰበብ የሚያገኘው ሥንጥቅ ትርፍ ናላውን እያዞረው በጥጋብ ከበር መልስ ቸበር ቻቻ ማለቱ የዕድገትና የብልጽግና ሳይሆን የኪሣራ ምልክት ስለሆነ በፍጥነት አንድ ነገር ካልተደረገ - በተለይ ዲያስፖራው ይወቀው - ሀገራችን እንደ ሀገር የመቀጠልዋ ተስፋ ቃላት ሊገልጹት ከሚችሉት በላይ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሶኣል:: ለነገሩ አምና «የክብሬ መመኪያ. . .» እያለ መድረክ ላይ በሀገርና በሕዝብ ፍቅር «ተቃጥሎ» መንታ መንታ ሲያነባና ሲያስነባ የነበረ አርቲስት አፍታም ሳይቆይ ባመቱ ኢንቬስትመንት ላይ ቢውል የስንቶችን ወስፋት ሊሸነግል የሚችልን ብዙ ገንዘብ ለጉራ ሲባል ብቻ **ሐመር** መኪና የሚገዛና በዚያም ሳይመለስ «ዘፈኔን ከወያኔ በቀር የተቃዋሚ ፖለቲከኞች ለምርጫ ቅስቀሣ መጠቀም አልነበረባቸውም» የሚል ጉደኛ የሕዝብ ሰው(A man of the People, cf. Chinua Achebe’s creative works) በሚፈልቅባት ኢትዮጵያችን አሁን ያለው ዝብርቅርቅ ማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ላያስገርም ይችላል:: ይሄ ሆድ የሚሉት ነገር እንኩዋንስ በበስተኋላችን አልሆነ- ገፍትሮ ገደል ይከተን ነበራ! ለማንኛውም የኑሮ ውድነቱ በዚህ መልክ ከቀጠለ በቅርቡ ከፍተኛ ማኅበራዊ ቀውስና በውጤቱም በቀላሉ የማይበርድ ሀገራዊ ትርምስ ሊፈጠር እንደሚችል መገንዘብ ይኖርብናል:: <u>ስለሆነም ሀገር አለኝ የሚልና የኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባኛል የሚል ኢትዮጵያዊ ዜጋም ሆነ ማንኛውም ሰብኣዊ ፍጡር የጥቂት ወሮበሎች እንደልብ መፈንጪያ የሆነችው «ኢትዮጵያ» የምትባል ሀገር ከነሕዘብዋ መቀመቅ ሳትወርድ አሁኑኑ ይድረስላት::</u> የዚች ጽሑፌ እምብርት መልዕክት ይህ ያሠመርኩበት ሃሳብ ይሁንልኝ:: ወደ ሌላ ዋና ጉዳይ ላኮብኩብ::

በአንዳንድ ነቃ ያሉ የቢዝነስ ተቋማትና ሆቴሎች ግድግዳዎች ላይ «ደካማ ጎናችንን ለእኛ፤ ጠንካራ ጎናችንን ለሌሎች ይንገሩ» የሚል ማስታወቂያ ተጽፎ አያለሁ:: ቆንጆ ነው:: ሂስና ግለ ሂስ እንደጦር በሚፈሩባቸው፣ «ፊትህ ላይ ያለውን ጉድፍ ቢጤ አስወግደው» ቢባል በ«ምን አገባህ?»ና በ«እንዴት ተደፈርኩ!» ስሜት ሳቢያ የሸሚዙን እጅጌ ለቀለጠ አምባጉዋሮ የሚሰበስበው ወገናችን ቁጥር ጥቂት ባልሆነበትና ከልሂቅ እስከ ደቂቅ ትችትን በአሉታዊ ጎኑ የጎሪጥ የሚመለከተው የተማረም ሆነ ያልተማረ የኅብረተሰብ ክፍል በሞላባት ሀገራችን ውስጥ ያን የመሰለ ማስታወቂያ ቢለጠፍ አይገርምም:: በሁሉም ማኅበራዊም ሆነ ፖለቲካዊ ሕይወታችን ውስጥ የሚንጸባረቀው መራር እውነትም ይሄው ነው::

በሀገራችን ለዘመናትና እስካሁንም ድረስ ነግሦ የሚታየው የመሞከሻሸትና የመሞጋገስ ባህል ነው። የጎንዮሽ ትንሽ - እንዲያው በስህተት ላመል ታህል - ነቀፌታ ብትሰነዝር ዓለም ታልፋለች- አርማጌዶን ይነሳል። «አካኪ ዘራፍ! ማን ነው ወንዱ!» ባዩ ይበዛል። ለነገሩ በ«ውረድ እንውረድ ተባባሉና. . .» የፉከራ ባህል ውስጥ ያደገ ትውልድ ትችት ወይ አቃቂር ሊያውም በቅጡ ባልተገራ አንደበት ቢሠነዘርበትና ከስድብና ከዱላ ቢቆጥረው ብዙም አይፈረድበትም። የአስተዳደጋችን መስተጋብር እጅግ በርካታ አወንታዊ ጎኖች የመያዙን ያህል ካለማበል በግልጽ እንነጋገር ከተባለ አያሌ ሕፀፆችም እንዳሉበት በረባ ባልረባው የምንራኮትበትና ከሀገርና ከሕዝብ ተራ የወጣንበት ወቅታዊ ኑባሬያችን ለማንም ሳያጋድል እውነቱን ይመሠክራል። አትንኩኝ ባይነት አጉል ወኔ ሰቅዞ የያዘን ወገኖች ቁጥር በአሁኑ ወቅት ቀላል አይደለም፤ ይህ አሳሳቢ ጎጂ ባህላችን በተጠየቃዊ አመክንዮና ምክንያታዊ መሸናነፍ ካልተተካ ዕድለኞች ከሆንን ባለንበት እንረግጣለን - ከባሰብን ግን በጀመርነው የመጠፋፋት አባዜ ሁላችን ተያይዘን ወደሚቀርበን እንጦርጦስ እንወርዳለን። ምርጫው የራሳችን ነው - ተያይዞ መጥፋት ወይም እንደሕዝብም እንደሀገርም እስካሁን ስንጓዝበት የነበረውን አቅጣጫ ቆም ብለን በመመርመር ሌሎች ሀገሮችና ሕዝቦች ያደረጉትን የአስተሳሰብና የአመለካከት ለውጥ በድፍረት አካሂደን በአዲስ ርዕዮት ራሳችንን ማስተካከልና አስተሳሰባችንን ማዘመን ነው። አለበለዚያ ሥራችን ሁሉ ውሀ መውቀጥ ነው - ላይልም ላይሰለቅ።

በብሶት ጎዳና እዬነጎደ ያለ ሰው የመጣለትን ቢናገር የሚፈርድበት ሰው አይኖርም ብዬ አምናለሁ - እዬዬም ሲዳላ ነው አሉ። ቀዳሲያን ካህናት «ንግባኢኬ ሃበ ጥንተ ነገር» እንዲሉ እኔም ወደ ቀደመው ነገሬ ወደ እህቴ ሃሳብ ልመለስ - በነገራችን ላይ ስምዋን መጥቀስ ያልፈለግሁት ፈቃድዋን ስላልጠየቅሁ ለደኅንነትዋ ስል ነው፤ ምንም እንኩዋን ከኢትዮጵያ ውጭ ብትኖር መጠርጠር ደግ ነው - ‘ያልጠረጠረ ተመነጠረ‘ አይደል የምንል? የወያኔ እጅ ለውድመት ከሆነ ረጂም መሆኑን አውቃለሁ። አይደለም ጂቡቲ ሩቅ ምሥራቅ ጃፓንና አላስካ አሜሪካ ድረስ የጥፋት ወንጭፉን በመወንጨፍና በማስወንጨፍ በዜጎች ላይ ጉዳት ከማድረስ አይመለስም - በተደጋጋሚ ታይቷልም። እንዲያው ግን ግን - እንደወያኔ ያለ የጥፋት ልዑክ በሰው ልጆች ታሪክ ታይቶና ተሰምቶ ያውቅ ይሆን? እስኪ በእግዚኣብሔር ይሁንባችሁና የምታውቁት ካለ በኢሜል አድራሻየ ላኩልኝ።

እታለም የምትለን «የሲቭክ ማህበራት ወይም ሌሎች ተመሳሳይ ድርጅቶች አጠቃላይ የጸሎት ጥሪ ቢያደርጉ» ነው። እኔ ደግሞ ይህ ዓይነቱ በጋራ ወደ እግዚአብሔርም ሆነ ወደ አላህ የመጸለይ ቅንጦት በኢትዮጵያ ምድር አይታሰብም የሚል ነው። ነገሩ እንዲህ ነው - ቀላሉን ጉዳይ አጦዝከው እንዳትሉኝ። በኢትየጵያ ውስጥ ለኢትዮጵያ፣ ፈጣሪ ሰላሙን እንዲያወርድላትና መረጋጋትን እንዲሰጣት ለመጸለይ መሞከር ቄስም ሆንክ ምዕመን ወይም የደብር አለቃ - ደረሳና ቃልቻም ሆንክ ሼኽና ኢማም ከቤተስኪያን ወይም ከመስጂድ ስትወጣ የሚጠብቅህን ማወቅ አለብህ። በመጀመሪያ ደረጃ የምትጠየቀው ጥያቄ « ምን ለማለት ፈልገህ ነው? በሀገራችን ሰላም የለም ያለህ ማን ነው? አሁን ካለው መረጋጋት በላይ ምን ዓይነት መረጋጋትና ሰላም ይምጣልህ? አንተ የዱሮ ሥርዓት ናፋቂ!. . .» ትባልና ከፍተኛ የቃል ማስጠንቀቂያ ይሰጥሃል- የፓርቲ ታርጋም ቢለጠፍብህ መቻል ነው- ግንቦት ሰባት፣ ቅንጅት፣ አንድነት፣ ወዘተ. ልትባል ትችላለህ፤ ደግሞም ዕድሜ ሀገራችን ላፈራቻቸው ሥፍር ቁጥር የሌላቸው የፓርቲ፣ የግምባርና የንቅናቄ ስሞች የሚለጠፍ ነገር መች ይጠፋና። የቅድሚያ ማስጠንቀቂያው የሚሰጥህ በየማምለኪያ ሥፍራዎቹ የበግ ለምድ ለብሰው ከተሰገሰጉት የወያኔ ተላላኪ ተኩላዎች ነው። ነገሩ ከባድ ነው ጎበዝ - እነዚህ ሰዎች ያልመጡብን አቅጣጫ የለም። በሀገራችንና በአንድነታችን ብቻ ሳይሆን ለዘመናት አስተሳስሮ ባቆየን ሃይማኖታችንም ልብሰ ተክህኖ እየለበሱና የሃሰት ቆብ እየደፉ - ነአኩተከንና አቡነ ዘበሰማያትን እንኩዋን የማያውቁ “ካህናትና ጳጳሳት” ከዋናው አባታችን ጀምሮ (<u>በቃለ እግዚሃሩስ እሳቸው አይታሙም፤ ለተልዕኮኣቸው ስኬት ሲሉ መልከ ሳጥናኤልን ደረቡበት እንጂ</u>) ምንና እንዴት መጸለይ እንዳለብን መመሪያ ወጥቶልን ነው በነሱው መርሐ ግብር መሠረት የምንጸልየው። ከዚያች ውልፊት ማለት ቅጽፈት ነው ወገኖቼ። በዉጭ ሀገሮች ያላችሁ ቢያንስ ከዚህ ዓይነቱ የጸሎት ገደብና ማዕቀብ ስለተገላገላችሁ የልባችሁን ሲሻችሁ ባንድነት ሲሻችሁ በግል ልትጸልዩ ይቻላችሁዋል። ታድላችሁ! እናም በኛ ላይ የተጣለው የአትጸልዩ ማዕቀብ እስኪነሣልን (ለነገሩ ወያኔ እስካለ የሚነሣልንም አይመስለኝም) እናንተበርትታችሁ ጸልዩ - «ሁለት ባላችሁበት ሦስተኛ እኔ አለሁ» እንዲል መጽሐፉ። ለእኛ አሁን አሁን የቀራቸው የሚመስለኝ - «የአቡነ ተ/ሃይማኖት ቤ/ክርስቲያን ለአማሮች፣ የአቡነ አረጋዊ ለትግራዉያን፣ የቅድስት ክርስቶስ ሠምራ ለሸዋ ሮቢትና አካባቢዋ . . .» ብለው ታቦቶቹንም በጎሳና በዘር ከፋፍለው እንዳይመድቡልን ነው ፍራቻየ። ሌላው ሁሉ ሆንዋል። ምንም የማያውቁ ግዑዝ

ነገሮች አለአበሳቸው የዘር ሐረግ አመልካች ቅጽል ተለጥፎባቸው የምታሳዝን ገበያ አገልጋይ ጣሊያን ሥሪት ሎንቺና ዱሮ አማራ ትግሬ ሳትል ቆላ ደጋ ስትባዝን እንዳልነበር ዛሬ በፊት ለፊቷና በስተጀርባዋ «ኦሮ/አማ/ትግ/ደሕ . . .» የሚል የዘር ታርጋ ተለጥፎላትና በለመደችው ቦታ ሁሉ እንደልቡዋ ተዘዋውራ የመሥራት ዕድል ተነፍጓዋት ስትመለከቱ ቅስማችሁ ስብር ብሎ ታዝኑላታችሁ:: እኛም እንደ 666 የጋንኤል ቁጥር ግምባራችን ወይም እጃችን ላይ ገና አልተለጠፈብንም እንጂ መታወቂያችንን ጨምሮ በዬመዝገባችን የዘር ታርጋ ተለጥፎልናል:: ይሄ አሠራርም በመንግሥት ሥራዎች ለመቀጠር፣ የንግድ ሸቀጥን ያለግብርና ቀረጥ ያለቆንጣጭና ያለገልማጭ እንደልብ ከቦታ ቦታ ለማዘዋወርና ለመሸጥ፣ለክትትል፣ ሹም ሽር ፣ ለአባላት ምልመላ፣ ብቻ ምን አለፋችሁ . . . ለነገሩ የምታውቁትን ምን አዘበዘበኝ?

ወደ ተነሳሁበት ጉዳይ ገባሁ:: እናም ብፁዕ አባታችንም ( የኢት/ኦር/ቤ/ፓትርያርክ፣ የመንበረ ተ/ሃይማኖት ዕጨጌ፣ የአክሱም ጽዮን ሊቀ ጳጳስ፣ የዓለም አ/ክ ፕሬዚደንትና የዓለም ቤ/ክ ኅብረት የቦርድ ሰብሳቢ(ይቅርታ እዚህ ስደርስ ሥልጣናቸው ጠፋኝ- ሌሁም እኔው ሆኜ!) ይሄ ሁሉ በደል በቤተክርስቲያንና በሕዝብ ላይ ሲደርስ እያዩ ተጨማሪ መውገሪያ አሎሎ በማቀበል ከመተባበር በስተቀር ለማስቆም አልሞከሩም:: በዚያ ላይ ብፁዕ ጣዖትነታቸው ከጥንት ጀምሮ የሚያደርጉትን ስናይ ለተገቢው ዝርጠጣየ ይቅርታ ይደረግልኝና ከቅዱስነት ይልቅ ለርኩስነት ይቀርባሉ ቢባል ከእውነት መራቅ አይሆንም:: እሳቸውን ሳስብ አንድ አጠገቤ የሚገኝ መጽሐፍ ውስጥ ያነበብኩት በ15ኛው መቶ ክፍል ዘመን የሮማ ካቶሊክ ሊቀ ጳጳስ የነበረ አቡነ ሮደሪጎ የሚባል ሞሽላቃ ሌባ ፊቴ ላይ ድቅን ይልብኛል- ሰይጣን ክብር አያስፈልገውም ብዬ ስለማምን ግዴላችሁም ባነጋገሬ አይሸክካችሁ:: ያ ሌባ ሰውዬ ሦስት በጥንግ ድርቡ ሥር የወለዳቸውን የኃጢያት ፍሬዎቹን በማን አለብኝነት በግዛቱ ውስጥ ትላልቅ የሥልጣን ቦታ ሰጥቶ በገሃድ ሾሙዋቸዋል:: ስለኛዎቹም ጉዶች ብዙ ማለት ይቻላል - ለጊዜው በይደር ላስቀምጠው:: ይሁንና ግና «ቀበጥ አማት ሲሶ ብትር አላት» እንዲሉ ነውና የበደል ጽዋው ሞልቶ እየፈሰሰ ያለው የወያኔ ወንጀልና ኃጢያት ቋቱን ሞልቶ ለዕኩያን አባላቱ ብድራቱ በሠፈሩት ቁና ሲሠፈር እነሱም - እነአባ እና እነሌሎቹም - ምን ስም አስጠራኝ - የሃይማኖት አባት ተብዬዎች(ወይ አለማፈር እናንተዬ!) በድብቅ ለሠሩት ደባና ተንኮል ሳይቀር እንደዬድርሻቸው መቁነናቸውን እንደሚቀበሉ ልንጠራጠር አይገባንም:: «በሰው ኃጢያት አንተን ምን አገባህ?» ለምትሉኝ « ስለ መለስስ ለማውራት ማን ሥልጣን ሰጠን?» የሚለው አንደበቴን የማሙዋሸበት የመጀመሪያው መልሴ ይሆናል:: አዎ፤ «አትመራመር፤ትቀሰፋለህ!»ና «ሰማይ አይታረስ፤ ንጉሥ አይከሰስ» በሚሉ ከፈጣሪ ያልመጡና ለነሱ መሠሪ ዓላማ ብቻ በሚያገለግሉ ማደንዘዣዎች አማካነት ከተፈጥሮ ዕውቀቱ ውጪ እምብዝም ዘመናዊ ትምህርትና አስተሳሰብ የሌለውን ሕዝባችንን ለዘመናት ማነሁለላቸውና በሥልጣኔ ከዓለም ሀገሮች ዉራ እንዲወጣ የበኩላቸውን አስተዋፅዖ ማድረጋቸው ሳያንስ ከመጣው መንግሥት ጋር ሁሉ እየተሻረኩ በሁለት ቢላዎ መብላታቸው በራሱ ከኃጥኣን ጎራ ያስመድባቸዋል:: በአቡነ ጴጥሮስ መንበር የወርቅና የነሐስ ሐውልት ሠርታችሁ ከፈጣሪ በላይ አምልኩኝ የሚሉን ጣዖትነታቸው ብፁዕ አባታችን የማፈሪያ አዕምሮኣዊ ክፍላቸውን የባሕርይ አባታቸው የሆነው የቀድሞው ሊቀ መላእክት ሣጥናኤል ስለነጠቃቸው በስተርጅና የሚሰሩትን አጥተዋል:: ለትክክለኛው ሃይማኖታዊ ቃለ ዐዋዲ አንገታቸውን ለሠይፍ ደረታቸውን ለጦር የሰጡ እንደነመጥምቁ ዮሐንስና በሀገራችንም እንደነአቡነ ጴጥሮስ ያሉ እውነተኛ የሃይማኖት አባቶችና ወንጌላውያን በነበሩባት ቤተ ክርስቲያን አሁን መጭና እንክርዳድ በቅሎባት የአጋንንት መቦረቂያ ስትሆን ማየት ልብን የሚሰብር የክፍለ ዘመኑ ታላቅ ሀዘን ነው:: እናም እነዚህ ከበዳዮችና ከግፈኞች ጋር እየተመሣጠሩ በጎቻቸውን በተኩላና በቀበሮ የሚያስጨርሱ ዋልጌ የሃይማኖት «እረኞች» ሳይቀጡ የሚቀሩ የሚመስለው ካለ ፍጹም የዋህነት ነው:: «ቆሞ ያለ የሚመስለው ይጠንቀቅ» ይላል ሐዋርያው ቅዱስ **ጳውሎስ** ('ስም አይገዛም' የሚሉት ተረት እንዴት ያለ ሃቅ ነው 'ባካችሁ?) :: ከአሁን ወዲያ ማላገጥ የለም:: የብድራት መክፈያው ጊዜ እንደደረሰ በበኩሌ ሚጢጢዬዋ «ሦስተኛዋ ዐይኔ» ሹክ እያለችኝ እንደሆነ ይሰማኛል:: «በሠፈሩት ቁና መሠፈር» ደግሞ ሳይታለም የተፈታና የማይገዳደሩት ዘላለማዊ እውነት መሆኑ የሁላችን ግንዛቤ ይመስለኛል::

ከፍ ሲል ለመግለጽ እንደሞከርኩት በኢትዮጵያችን ውስጥ ጸሎትም በመቁነን ነው ውድ ምዕመናን፤ ስለፈለጉት ጉዳይ መጸለይ ሃራም ነው - የማይፈቀድና የተከለከለ፤ የማይቻልና የሚያስቀጣ:: እንጂ እንደዚያ ቢቻል እንደ ጥንት እንደ ጡዋቱ - ሕጻናትና ጥጆች እንዳይጠቡ ተደርጎ ሰው ሁሉ ባንድነት በዬቀየው ወይም በዬአጥቢያ ቤ/ክርስቲያኑና በየመስጂዱ ተሰባስቦ «እግዚኦ መሐረነ . . . ፈጥረህ አትርሳን . . . የቀን ጅብ በልቶ ጨረሰን. . . እንደበፊቱ አንድ አድርጎ በርኅራሄና በሀገር ፍቅር ስሜት የሚያስተዳድር ደገኛ መንግሥት ስጠን . . . በዘርና በጎሳ የማይከፋፍል፣ በድህነታችን የማይሳለቅ፣ በሞታችን ለመበልጸግ የማይጥር፣ በአሣራችን የማይደሰት፣ በነፍሰ ሥጋችን

የማይጫወት፣ አንጡራ ሀብት ንብረታችንንና መሬታችንን በወለድ አግድ ለውጭዎች ባገኘው ዋጋ እየቸበቸበ ለከፋ ድህነት የማያጋልጠን፣ አዋርዶ ላዋራጅ አሳልፎ የማይሰጠን፣. . . ሃይማኖት ያለው መሪ ስጠን፤ እኛንም አንድ ልብ ስጠን፤ ከስህተታችን አስተምረህ ሁላችንን ወደሚጠቅም የጋሪዮሽ አመለካከትና አስተሳሰብ መልሰን፤ ለመሠሪዎችና ለከፋፋዮች የአጥፍቶ ጠፊ አገዛዝ ምቹ እንድንሆን አታድርገን፤ ለዘመናት ያንገፈገፈንን የጭቆና ቀምበር አንስተህ ሊመለስ ወደማይችልበት ሩቅ ሥፍራ ወርውርልንና በቃችሁ በለን፤ ስደትንና ጦርነትን፣ ርሃብንና ተንኮል ምቀኝነትን ከሀገራችን አጥፋልን . . . » ብለን በአንድ ልብ ኪሪያላይሶኣችንንና ዱኣችንን ወደ ላይኛው ብንሰድ የኢትዮጵያ አምላክ አፍታ አይፈጅበትም፡፡ (እዚህ ላይ ጸሎት ለሚያምንበት አጋዥ መንፈሳዊ ኃይል እንጂ ብቸኛው አማራጭ ሊሆን እንደማይችል መረዳት ይገባል፡፡ መጽሐፉ የሚለው ‘ጥረህ ግረህ በላብህ’ ብላ እንጂ መና ከሰማይ ይላክልሃል አንጋጠህ ጠብቅ አይደለምና) ነገር ግን በአንድ ልብ ሆነን ይህንን አሁን ለማድረግ እንዳንችል በብዙ ነገር ተለያይተናል፡፡ ሌላው ቀርቶ በአንድ ቤት ውስጥ እንኳዋን ሠላሳ (ነገር በጥቂቱ ካልተጋነነ አይጣፍጥም ‘ባካችሁ) ሃማኖት እንዳሽን እየፈላ አባወራና እማወራ የቤተሰባቸውን ሥጋዊና መንፈሳዊ ሕይዎት መለዬት ያቃታቸው ጊዜ ላይ ነው የምንገኘው - ሃይማኖት የግል ጉዳይ መሆኑ እንዳለ ሆኖ፡፡ በሌላ በኩል ያለውንማ ልዩነት መተው ነው የሚሻል፡፡ በሀብት ክፍፍል ረገድ የሚታየውን የሀብታምነትና የድህነት ደረጃዎች፣ በነጋዴውና በሸማቹ መካከል ያለው ፍጹም መረን የለቀቀና ከማንኛውም ዓለማቀፍ ሕግ በሀገራችን ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ በእጅጉ ያፈነገጠ የንግድ ግንኙነት (አንዳንድ ነጋዴ እኮ አንጎል ያለውም አይመስልም - ሕዝብን በደረቁ ላጭቶ ባንድ ሌሊት ሲቶጀር- ቱጃር ሰሆን-) ፣ ሕዝብን ሊያገለግል በመንግሥት ሥልጣን ላይ ተቀምጦ መነኩሲቷን ሳይቀር «ምርኩዝዎን ሽጠውም ቢሆን በእጅዎ ካልመጡ በቀር በእግርዎ መጥተው ጉዳይዎ አያልቅም» ሊል የሚቃጣውን ሆዳም ሙሰኛና ሌላ ሌላውን ጉዳችንን ከተመለከትን ተስፋ መቁረጣችን አይቀርም፡፡ ልዩነቶቻችን በተራው የዕለት ተለት ኑሮኣችን ውስጥ ሳይቀር የትዬለሌ ናቸው፡፡ ልብ አድርጉ እንግዲህ- እኛ እስከዚህ ተለያይተን የምንጨብጠውንና የምንለቀውን ካጣን ከኛ ውጪ ያለ መንፈሳዊ ኀላዌ እንዴት አድርጎ ነው ከእኛ በላይ ስለኛ ሊጨነቅና እኛ ያልተወጣነውን ኃላፊነት እንዲወጣ ልናስገድደው የሚቻለን? በመጀመሪያ የኛን ግዴታ መወጣት አይኖርብንም ብላችሁ ታስባላችሁ? ስለዚህ ለጸሎት በጋራም ሆነ በቡድን መትጋታችን ከዋነኛነት ጉዳይ ባልተናነሰ መልኩ እንዳለ ሆኖ የዬግል ጉድፋችንን ዉለን ሳናድር ማበስና አዲስ ስብዕና መላበስ ይኖርብናል፤ አለበለዚያ ቀደም ሲል እንደተባለው ያው ወሃ መውቀጥ ነው ትርፉ፡፡ አሁን ብዙዎቻችን ችግራችንን አናውቅም የሚል ግምት የለኝም፡፡ ጭንቀታችን የመፍትሔው ጉዳይ ነው የሚመስለኝ፡፡ መፍትሔውን ያራቅነውም እኛው ነን፤ ተጠቅመን ሳንጠቀምባቸው አንዳንዶቻችን ባሉን ልዩነቶች ላይ ባውዛ አበራንባቸውና- እንዲያው ሲያቀብጠን - እዬቆየን የቀባጭ ምሳችንን ማግኘታችን የማይቀርልን መጥፎ ዕጣ ሆነብን፡፡ ታዲያ አሁን ምን ማድረግ ይበጀናል? መፍትሔው እጅግ በጣም ቀላል ነው፡፡ [የአእምሮ ችግር እንደደረሰበት - አንፍረድበት ባካችሁን - የማምነው ሶሎሞን ተካልኝ ለአቶ መለስ ትክለ ሰውነትና የአመራር ችሎታ በቅርቡ እንዳቀነቀነው ዓይነት] አሥር አለቃ ዉቢሻሽ(?) ለሊቀ መንበር መንግሥቱ «ለቆራጡ መሪ» ብላ ያቀነቀነቸዋ ድምጻዊ « ትግል ከራስ» ብላ ያንጎራጎረችው ሌላ ዘፈን አሁን ድረስ ትዝ ይለኛል፤ መልዕክቱ ጥሩ ነው፡፡ ማንኛውም የለውጥ ትግል መጀመር ያለበት ከራስ መሆኑን በዘፈንዋ ገልጻለች፡፡ ስለዚህ በሰው ከመፍረዳችን በፊት ራሳችንን በአወንታዊ መልክ ብንለውጥ የመጀመሪያዎቹ ተጠቃሚዎች እኛው ራሳችን ነን፡፡ በሰው ዐይን ውስጥ ያለውን ጉድፍ ማየት ቀላል ሊሆን ይችላል- በቅድሚያ በራሳችን ዐይን ውስጥ ተጋድሞ የሚገኘውን ግን መቆርቆሩ እንዳይሰማን ችላ ብለን የተውነውን ዕርፍ እሚያህል ጉድፍ ማውጣት ይገባናል፤ እንደ ታላቁ መጽሐፍ አስተምህሮ፡፡ ከጅቡቲዋ በተላከችልኝ ማስታወሻ የነገር መነሾ ጥቂት ማዉራት በመቻሌ አንባቢንና አንቺን እህቴን እያመሰገንኩ ልሰናበት፡፡ መሰልቸት ብሎ ነገር የለም፤የሚጽፍ ሳይታክት ይጻፍ፤ «የወለዱትን ያልሳሙለት፤ ያቀረቡትን ያልበሉለት» ይባላልና ማንበብ ግን የሁላችንም ግዴታ ይሁን፡፡ ያለለት እልም ባለ የጨበጣ ውጊያ ውስጥ ገብቶ ለሀገሩ ነጻነት ሲል በጥይትና በሣንጃ ይተጋተጋል - እኛ ደግሞ ቢያንስ ቁርጥራጭ መጣጥፎችን ከድረ ገፆች ባማረ ወንበር (ደግሞስ ባያምርስ?) ላይ ተቀምጠን በማንበብ ስለሀገራችን ወቅታዊ ጉዳይ ግንዛቤ መጨበጥ የሚያቅተን አይመስለኝም፡፡ ቸር ይግጠመን፡፡

yiheyisaemro@gmail.com